# በቤት ውስጥ
# የደህንነ ስሜት እንዲሰማዎ
# መብት አለዎት

Queensland Government

በአውስትራሊያ ውስጥ የቤት እና ቤተሰብ ሁከት መፍጠር ተቀባይነት የለውም። ማንም ይሁኑ ወይም ከየትም ይምጡ ችግር ማንም ላይ ሊደርስ ይችላል እንዲሁም በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ያለ ችግር ነው።

**በመጥፎ ሁኔታ ከተያዙ/ወይም በቤትዎ ውስጥ የሚፈሩ ከሆነ የርስዎ ጥፋት አይደለም። በዚህ ላይ ማፈር ወይም ቅር መሰኘት አይገባዎም።**

**ጤናማ የሆነ ግንኙነት ማለት ታማኝነት፣ ተደጋጋፊነትና ደህንነት ያለው ነው። ማንም በቤተሰቡ ውስጥ ያለን ሰው መፍራት የለበትም።**

**እርዳታ አለ ። ደህንነት ካልተሰማዎ እርዳታ መጠየቅ ተገቢ ነው። እርዳታ ሲፈልጉ እኛን ለማነጋገር:**

**ድንገተኛ ችግር (ፖሊስ ወይም አምቡላንስ)**
**በሶስት ዜሮ (000)**
የሆነ ሰው በድንገት አደጋ ከደረሰበት፡

**የሴቶች ለ 24 ሰዓት እርዳታ መስመር**
**(DVConnect) 1800 811 811**
በቤት ውስጥ ሁከት ላጋጠማቸው ሴቶች ያለክፍያ በነጻ፣ ሚስጢራዊነት ያለው ምክርና ድጋፍ ይቀርባል።

**የስደተኛ/ኢሚግራንት የሴቶች ድጋፍ አገልግሎት**
**07 3846 3490**
እንግሊዝኛ ከማይነገርበት አገር ለመጡ ሴቶች መማክርትና ምክር።

**የወንዶች እርዳታ መስመር (DVConnect)**
**1800 600 636**
ከትዳር አጋር እና የቤተሰብ ችግር ላጋጠማቸው ወንዶች ሚስጢራዊ የሆነ እርዳታ።

**ላይፍ ላይን/Lifeline**
**131 114**
በማንኛውም ጊዜ ቀንም ሆነ ማታ ግላዊ የሆነ ከባድ ችግር ካጋጠመዎ ድጋፍ።

Interpreter

በራስዎ ቋንቋ አስተርጓሚ ለመጠቀም በስልክ **13 74 68** መደወል።

**ለቤት ውስጥ እና ቤተሰብ ሁከት ፈጠራ ባህል በምንም መልኩ ምክንያት አይሆንም።**

**www.qld.gov.au/domesticviolence**

የቤት ውስጥ እና ቤተሰብ ሁከት የሚፈጠረው አንድ ሰው በግንኙነት ጊዜ ሌላውን ሰው በሃይል መቆጣጠር፤ ማጎሳቆል ወይም ማስፈራራትን በሚጠቀምበት ጊዜ ነው ። ብዙ የተለያዩ መልኮች ሲኖሩት ባብዛኛው የሚከሰተው በቤተሰብ ወይም በቤት ውስጥ ባለ ግንኙነት ነው።

## ባለቤትዎ፤ የቤተሰብ አባል ወይም እርስዎን የሚንከባከብ ሰው ከዚህ በታች ካሉት ማንኛውም ዓይነት ማጎሳቆል ከፈጸመ ወም ለመፈጸም ማስፈራሪያ ደርሶዎታል?

### የገንዘባዊ ጫና

- ሰርተው የሚያገኙትን ገንዘብ ወይም የሚፈቀድልዎን (የሴንተርሊንክ አበል) መውሰድ?
- ለርስዎና ለልጆችዎ ፍላጎት ማሟያ በቂ ገንዘብ አለመስጠት?
- ምን እንደሚገዙ መታዘብ እና መቆጣጠር?
- ሥራ እንዳያገኙ መከላከል?

### የአካል ድብደባ

- መግፋት፣ መምታት፣ ማነቅ፣ መርገጥ ወይም ወደርስዎ እቃዎችን መወርወር?
- ወደ ህክምና እንዳይሄዱ ማገድ ወይም በቂ ምግብና ውሀ እንዳያገኙ ማድረግ?

### ወሲባዊ በደል

- ሳይፈልጉ በግዴታ ወይም በኋይል ወሲብ እንዲፈጽሙ ማስገደድ (በትዳር ላይም ቢሆን)?
- ወሲብ ካልፈጸሙ ጉዳት ለማድረስ ማስፈራራት?

### ስድብ

- በርስዎ ላይ ጸያፍ የሆነ ቃላትን መጠቀም?
- በተለይ በህዝባዊ ቦታ ላይ እርስዎን ማዋረድ፣መተቸት ወይም መሳደብ?

### የስሜታዊና ስነ-ልቦናዊ ማጎሳቆል

- ዋጋ ቢስነት፣ ሀፍረት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ጭንቀት ወይም የፍርሃት መንፈስ እንዲያድርብዎ ማድረግ?
- የአካል ላይ ጉዳት በእርስዎ፣ በልጆችዎ፣ በቤተሰብ አባላት ወይም በቤት እንስሳትን ላይ ለማድርስ ማስፈራራት?
- ፓስፖርትዎን መደበቅ ወይንም ከአውስትራሊያ እንዲባረሩ አደርጋለሁ ብሎ ማስፈራራት?
- አብሬ አልኖርም ወይም ልጆቹን እወስዳለሁ በማለት ማስፈራራት?
- ምን እንደለበሱ፤ እንዳዩ እና/ወይም እንዳነበቡ መቆጣጠር?

### በባህላዊና በመንፈሳዊ እምነት ላይ ማጎሳቆል

- በባህላዊ ወይም በመንፈሳዊ እምነቶችወይም በልምዶችዎ ላይ እንዲያፍሩ ማድርግ?
- የመረጡትን ቋንቋ ከመጠቀም፣ ባህላዊ ወይም የሃይማኖት ድርጊቶች ወደሚካሄድበት ቦታ እንዳይሄዱ መከልከል?
- ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ እምነቶችን እንደ ምክንያት ተጠቅሞ እርስዎን መጉዳት ወይም ማድረግ የማይፈልጉትን ነገሮች እንዲያደርጉ ማስገደድ?
- ጥሎሽ ካልተከፈለ ብሎ ማስፈራራት?

### ማሕበራዊ ማጎሳቆል

- የት እንደሚሄዱ መቆጣጠር፤ ማንን እንዳዩ መቆጣጠር ወይም እቤት እዳይወጡ መቆለፍ ወይም ቤተሰብዎንና ጓደኞችዎን ከማየት ማገድ?
- የርስዎን ስልክ ጥሪዎችና ማሕበራዊ መገናኛን (ለምሳሌ፡ ፌስቡክ/Facebook፤ ኢንስታግራም/ Instagram) መቆጣጣር?
- ሌሎች ሰዎች ጋር ሲነጋገሩ መሰሰት እና መቅናት?

## ከነዚህ ነገሮች አንዱ በርስዎ ላይ ከደርሰብዎ፤ ይህ የቤት ውስጥ እና ቤተሰብ ሁከት ነው።